# ከምርጫ ቦርድ ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/

__አዲስ አበባ፣__

ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር 754/2002 በተፃፈ ደብዳቤ ፓርቲያችሁ ያቀረበውን አቤቱታ ቦርዱ በስፋትና በጥልቀት ከመረመረው በኋላ አንድም ተጨባጭ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ እስከ ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ እንድታቀርቡ ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር አ573/ፖአ/ጠ1605 በተፃፈ ደብዳቤ ማዘዙ ይታወቃል፡፡

ቦርዱ ለሰጠው ትዕዛዝ በቁጥር መለ3/760/2002 ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፋችሁት ደብዳቤ ከሐምሌ 3 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ ደረሰብን ያላችሁትን በደል በመዘርዘር 5 ገፅ በማያያዝ ለእነዚህም በደሎች ያስረዳሉ ያላችኋቸውን 50 ገፅ ያላቸው ሌሎች በደሎች ያላችኋቸውን በመጨመር ማስረጃየ ነው በማለት አቅርባችኋል፡፡

በመሠረቱ ቀደም ሲል ጀምሮ ላቀረብነው አቤቱታ ምንም ምላሽ አልተሰጠንም ያላችሁትን ጉዳይ በተመለከተ ቦርዱ በቅድመ ምርጫ ወቅት በተለያዩ ጊዜያት ፓርቲያችሁ ለሚያቀርበው አቤቱታ አግባብነት ያለው እና ተገቢ ሆኖ ያገኘውን የማጣራት ውጤት እያይዞ ምላሽ የሰጣችሁ እንደሆነ ካሉን ተጨባጭ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ምርጫው ነፃ፣ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እያለ ቦርዱ በሐቅ ሁላችሁንም በአንድ ዐይን እያገለገለ መሆኑን እያወቃችሁ ፓርቲያችሁ ምንም ነገር እንዳልተፈፀመ አስመስሎ ምርጫው ይደገም ለሚለው ጥቅል ክስ እንደምክንያት በማቅረቡ ቦርዱን በእጅጉ አሳዝኖታል፡፡

ፓርቲያችሁ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም መልስ ያልተሰጠበት አቤቱታ እንደሌለ እያወቀ ይህን መሰል ክስ ማቅረቡ ሕግና ሥርዓትን አክብረው ያስከብራሉ ከሚባሉ ፓርቲዎች የሚጠበቅ አካሄድ እንዳልሆነም ቦርዱ ለማስገንዘብ ይወዳል፡፡

በአጠቃላይ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር 754/2002 ለቦርዱ በተፃፈ ደብዳቤ ያቀረባችሁትን አቤቱታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንድታቀርቡ በታዘዛችሁት መሠረት ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. መለ/3/760/2002 በፃፋችሁት ደብዳቤ ያቀረባችሁትን ተጨማሪ አቤቱታ (ቦርዱ የጠየቀው ማስረጃ ቢሆንም) በጥልቀትና በስፋት መርምሮታል፡፡

በዚሁ መሠረት ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. የተካሄደውን አራተኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ በድጋሚ ለማካሄድ የሚያበቃ ምንም ዓይነት የሕግም ሆነ የአሠራር ግድፈት ስለመፈፀሙ በተጨባጭ ለማረጋገጥ አልቻላችሁም፡፡

ይህንኑ ያስረዳልናል ብላችሁ በተጨማሪም አባዝታችሁ ያቀረባችሁት አቤቱታ ከዚህ በታች በዝርዝር በገለፅነው መልኩ በወቅቱ በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ጽሕፈት ቤቶችና በቦርዱ ጭምር በጥንቃቄ ታይቶ መልስ የተሰጠበት መሆኑን እና ከዚህም ፓርቲያችሁ ተገቢውን ምላሽና አገልግሎት አግኝቶ ለምርጫው ውድድር ራሱን አዘጋጅቶ የገባ መሆኑን ቦርዱ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ካቀረባችሁት ተጨማሪ አቤቱታዎች ውስጥ የመራጮች እና የዕጩዎች ምዝገባን ጊዜ መራዘም በተመለከተ ቦርዱ እናንተን ጨምሮ ከሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተገናኝቶ በመወያየትና በመመካከር በይፋ ያወጣውን የጊዜ ሠሌዳ ጊዜ አጠረን ብላችሁ ባቀረባችሁት ጥያቄ መሠረት የዕጩዎችን ምዝገባ በቅድሚያ ለአሥር ቀናት በመቀጠልም ለሃያ ቀናት በጠቅላላው አንድ ወር ተጨማሪ ጊዜ አራዝሟል፡፡ በተጨማሪም በሁላችሁም ጥያቄ የመራጮችን ምዝገባ በመጀመሪያ

ለአሥር ቀናት በመቀጠልም በአምስት ቀናት በጠቅላላው ለአሥራ አምስት ቀናት እንዲራዘም አድርጓል፡፡

ከዚህ ውጪ በዕጩዎች ምዝገባ ላይ ቅሬታ የነበራችሁ ሲሆን የምርጫ ሕጉን ተከትላችሁ በወቅቱ ለሚመለከተው ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብና በየደረጃው መከታተል ሲገባችሁ በአሁን ደረጃ ለምርጫ ይደገም ጥያቄችሁ ማዳበሪያ ማድረጋችሁ ሕጋዊ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ምንም እንኳን ቦርዱ ከእናንተ ጋር በመወያየት ያወጣውን የጊዜ ሠሌዳ በራሱ ወጪ አሳትሞ ለሁላችሁም ያሠራጨው በኅዳር 2002 መሆኑ እየታወቀ፤ ወኪሎቻችሁንም በየምርጫ ጣቢያው ከምርጫው ቀን አሥር ቀን በፊት ለመመደብ አለመቻላችሁን ገልፃችሁ ከሌሎች ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ በኩል ባቀረባችሁት ጥያቄ መሠረት ቦርዱ ጥያቄያችሁን ተቀብሎ የምርጫው ቀን ሁለት ቀን እስኪቀረው ድረስ ማለትም እስከ ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ እንድታቀርቡ ወስኖ ይህንኑ ተከታትሎ አስፈፅሟል፡፡

በአጠቃላይ ቦርዱ እዚህ ውሣኔ ላይ ሊደርስ የቻለው ለተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምቹ የውድድር ሜዳ ለማዘጋጀት ካለው ቁርጠኝነት በመነጨ በምርጫው ሥራ ላይ የሚፈጠርበትን ጫና ባለው አቅምና ብቃት ለመቋቋም በመወሰኑ ነው፡፡

ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፋችሁት ደብዳቤ፤

**በተራ ቁጥር** 1. የገለፃችሁት ቦርዱ ሐምሌ 3 ቀን 2001 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/321/2001 በተፃፈ ደብዳቤ ጉዳዩን በግልባጭ እንዲያውቀው ያደረጋችሁ ቢሆንም በቀጥታ በአድራሻው የተፃፈለት የአማራ ክልል መንግሥት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩን በክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በኩል በምርጫ እንቅስቃሴያችሁ ችግር እንዳይገጥማችሁ የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ ሲደረግላችሁ መቆየቱን እናንተም የምታረጋግጡት ጉዳይ ነው፡፡

**በተራ ቁጥር** 2. ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. የፃፋችሁት ደብዳቤ በወቅቱ ቦርዱ አዘጋጅቶ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት ያቀረበው ረቂቅ የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳ ከሕዳር 15 እስከ ሰኔ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. እንዲሆን የሚጠይቅ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ረቂቅ የጊዜ ሠሌዳው ጥቅምት 14 ቀን 2002 ዓ.ም. በሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት ተካሂዶበት ምርጫው ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. እንዲካሄድ በመጨረሻ በአብዛኞቹ ፓርቲዎች በጋራ በተደረሰበት ስምምነት መሠረት ፀድቆ የወጣና ተግባራዊ የሆነ ነው፡፡

በመሆኑም ጥያቄያችሁ በጋራ ስምምነት ከተደረሰበት ውጪ የሆነ እና ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ በወቅቱ ተቀባይነት እንደሌለው ተገልጿል፡፡

**በተራ ቁጥር** 3. ኅዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም. ተፃፈ ያላችሁት ኅዳር 18 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ ደብዳቤ ነው፡፡ በዚሁ ደብዳቤ በየምርጫ ክልሉ የሚመደቡ የምርጫ ቦርድ ተወካዮችና በየምርጫ ጣቢያው ስለሚመረጡ ታዛቢዎች በተመለከተ ከገዥው ፓርቲ ጋር በተፈራረማችሁት እና 65 ፓርቲዎች ባፀደቁት ሰነድ መሠረት ነው ያላችሁት ያልደረሰን ከመሆኑም በላይ ግልፅነት የጎደለው እና የስነምግባር ሕጉም በወቅቱ ያልወጣ በመሆኑ ጥያቄያችሁ አግባብነት እንደሌለው ተገልፆላችኋል፡፡

የስነምግባር ሕጉም ከወጣ በኋላ ለአፈፃፀም ያቀረባችሁትን ጥያቄ በሕጉ ውስጥ ተካቶ እንደሆነ በቦርዱ ሲታይ አንዳችም ጉዳይ በተባለው መልኩ ተካቶ አልተገኘም፡፡

**በተራ ቁጥር** 4. ኅዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም. የሕዝብ ታዛቢዎችን ምርጫ አፈፃፀም በተመለከተ ላቀረብነው አቤቱታ መፍትሔ አልተሰጠንም ላላችሁት በመጀመሪያ ደረጃ የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ከመካሄዱ በፊት በየቀበሌው ወኪሎቻችሁን እንድታስቀምጡ ለሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በመገናኛ ብዙሃን ጥሪ ከታሕሣሥ 19 እስከ 21 ቀን 2002 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን በሁሉም የክልል ቋንቋዎች ተላልፏል፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ በሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ላይ

በየቀበሌው ወኪሎቻችሁን ልካችሁ እንድትከታተሉ በቦርዱ የተዘጋጀው የጥሪ ደብዳቤ ፓርቲያችሁ በወኪሉ አማካይነት በግንባር ተገኝቶ እና ፈርሞ ተረክቧል፡፡ ይኸውም፣

1. ታሕሣሥ 4 ቀን 2002 ዓ.ም. ለተካሄደው የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ዶ/ር ታዲዎስ ቦጋለ ሕዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ፈርመው ተረክበዋል፡፡

2. ታሕሣሥ 25 ቀን 2002 ዓ.ም. ለተካሄደው የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ ታሕሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም. የጥሪውን ደብዳቤ ፈርመው ተረክበዋል፡፡

በወቅቱ የተደረገላችሁን ጥሪ አክብራችሁ መገኘትና መከታተል የእናንተ ኃላፊነት መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው፡፡

ይህም ሆኖ የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እንዲደገም ጥያቄ በቀረበባቸው አካባቢዎች ቦርዱ በድጋሚ እንዲካሄድ አድርጓል፡፡ ይኸውም ቦርዱ በአዲስ አበባ ከተማ ካሉት 99 ቀበሌዎች ውስጥ በ58ቱ ላይ በድጋሚ የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ አካሂዷል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በሌሎች ክልሎችም ችግሩ ተከስቷል በተባለባቸው ቀበሌዎች ላይ በድጋሚ የሕዝብ ታዛቢ ምርጫ አካሂዷል፡፡ ፓርቲያችሁም በወቅቱ በሂደቱ ላይ እንደተገኘ አረጋግጠናል፡፡ ለምሣሌ መቀሌ፣ ገላና አባያ፣ ሚዛን ተፈሪ እና ወዘተ.

ስለሆነም መፍትሔ አልተሰጠንም ያላችሁት ከእውነት የራቀ ነው፡፡

**በተራ ቁጥር 5.** በተራ ቁጥር 3 ከፍ ብለን በዘረዘርነው መልኩ የቀረበ አቤቱታ ስለሆነ ጥያቄያችሁ አግባብነት እንደሌለው ተገልፆላችኋል፡፡

**በተራ ቁጥር 6.** በተራ ቁጥር 4 ከፍ ብለን በዘረዘርነው መልኩ የቀረበ አቤቱታ ስለሆነ ጥያቄያችሁ አግባብነት እንደሌለው ተገልፆላችኋል፡፡

**በተራ ቁጥር 7.** በመሠረቱ የካቲት 11 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/569/2002 ለቦርዱ የፃፋችሁት አቤቱታ የካቲት 9 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መኢአድ/ባ/ዳር/75-06-2002 ዓ.ም. በአድራሻው ለፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በግልባጭ ለአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እና ምዕራብ ጎጃም ምርጫ ጽሕፈት ቤት የተፃፈ ደብዳቤ መሆኑን በወቅቱ አረጋግጠናል፡፡

በዚሁ መሠረት ያቀረባችሁትን አቤቱታ ቦርዱ ሲያጣራ አቤቱታው ማስረጃ የሌለው እና ከእውነት የራቀ መሆኑን ከቀረበለት የማጣራት ሪፖርት እንዳረጋገጠ ሚያዝያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር አ573/ፖአ/ጠ/538 በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፆላችኋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ያለቀን ጉዳይ ምርጫው ከተካሄደ በኋላ እንደገና ማንሳቱ ምንም የሕግ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡

**በተራ ቁጥር 8.** የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/579/2002 በተፃፈ ደብዳቤ በመቱ እና በአሰላ የምርጫ ክልሎች በለቀቁት ዕጩዎቻችን ምትክ ተተኪ አቅርበን እንዳናስመዘግብ የምርጫ ክልል ኃላፊዎች ሕጉን ባለማክበር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል ብላችሁ አቅርባችኋል፡፡

በመሠረቱ በተጠቀሰው ደብዳቤ በወቅቱ የቀረበው አቤቱታ በመቱ እና በአሶሳ/በአሰላ ሳይሆን/ የምርጫ ክልል የሚል ነው፡፡

ይህም ሆኖ ከምርጫ ራሳቸውን ባገለሉ ዕጩዎች ምትክ ሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተተኪ ዕጩዎችን እያቀረቡ እንዲያስመዘግቡ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ በኩል ለቦርዱ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት በቂ ጊዜ ተሰጥቶ ምዝገባው በቦርዱ የቅርብ ክትትል እየተደረገበት ተፈፅሟል፡፡

ፓርቲያችሁ በዚህ በተሰጠው ተጨማሪ የመተኪያ ጊዜ ዋነኛ ተጠቃሚ እንደነበር እና ለዚሁም በይፋ ምስጋናውን ለቦርዱ እንዳቀረበ እናንተም የምታረጋግጡት ጉዳይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ በስተመጨረሻም ላይ ቢሆን በቦርዱ አልተፈቱልንም ብላችሁ ለሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጭምር ያቀረባችኋቸው እና በየጊዜው በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ በኩል ክትትል ተደርጎ አግባብነት ያላቸው ታይተው መፍትሔ የተሰጠባቸው አቤቱታዎች ውስጥ አሁን ያላችሁት ጉዳይ ተካቶ የሚገኝ አይደለም፡፡

ይህ ደግሞ የሚያሳየው ያቀረባችሁት አቤቱታ አግባብነት ያለው ምላሽ ያገኘ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ማሳያው፣

1. በአሶሳ መገሌ የምርጫ ክልል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

- ☐ አቶ ካሣሁን አራጋው አመዴ የመኢአድ ዕጩ ሆነው ተወዳድረዋል፡፡

2. በአሶሳ ሆሃ የምርጫ ክልል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

- ☐ አቶ ብሩ ዲሲሳ ጊዲቶ የመኢአድ ዕጩ ሆነው ተወዳድረዋል፡፡

3. በአሶሳ ወረዳ ለክልል ምክር ቤት፣

- ☐ አቶ አሳድቅ አልማሂ ኢሣ
- ☐ አቶ አብዱራዛቅ ሙሣ ዑስማን
- ☐ አቶ ኢብራሂም አወል ጫኔ
- ☐ አቶ አብዱልበጊ ከማል አሳድቅ
- ☐ አቶ ከድር አያሌው ኑራ
- ☐ አቶ ሰኢድ ገበየሁ አሊ

የመኢአድ ዕጩ ሆነው ተወዳድረዋል፡፡

4. በመቴ የምርጫ ክልል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

- ☐ አቶ ታሪኩ ፀጋዬ ለማ የመኢአድ ዕጩ ሆነው ተወዳድረዋል፡፡

5. በመቴ የምርጫ ክልል ለክልል ምክር ቤት፣

- ☐ አቶ ትክሳ ስንታየሁ ገብሬ የመኢአድ ዕጩ ሆነው ተወዳድረዋል፡፡

ስለሆነም ላቀረብነው አቤቱታ መልስ አልተሰጠንም ያላችሁት ፍፁም ከእውነት የራቀ መሆኑን ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

**በተራ ቁጥር 9**. የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/584/2002 ዓ.ም. ላቀረብነው አቤቱታ መፍትሔ አልተሰጠንም ያላችሁት ያቀረባችኋቸው አቤቱታዎች በምርጫ ሕጉ መሠረት በየደረጃው በሚገኙ በምርጫ ክልል እና በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በኩል አግባብነት ያለው ምላሽ የተሰጣችሁ እንደሆነ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር ኦሮ/ምቦ/65/02 በተፃፈ ደብዳቤ ምላሽ እንደተሰጣችሁ ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

**በተራ ቁጥር 10**. የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/591/20002 ላቀረብነው አቤቱታ መልስ አልተሰጠንም ያላችሁት ያቀረባችኋቸው አቤቱታዎች በምርጫ ሕጉ መሠረት በዝዋይና በመቂ የምርጫ ክልሎች አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎች በዝርዝር ታይቶ መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር ዝምክ/26/2002 በተፃፈ ቃለጉባኤ ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ይኸው ውሣኔ ሲሰጥ፣

1. አቶ ኢጀሮ ኤደሳ ቱጊ የመኢአድ የክልል ምክር ቤት ዕጩ፣
2. አቶ ከድር መሐመድ ሻቡሬ የመኢአድ የክልል ምክር ቤት ዕጩ

3. አቶ ዲክሲሶ ገለቶ ባቲ የኢራፓ የክልል ምክር ቤት ዕጩ
4. አቶ ደረሰ ዳባ ደበሌ የኢዴፓ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዕጩ
5. አቶ ትቤሶ ቀንቢ የኦሕዴድ የምርጫ ክልሉ የዕጩዎች ተወካይ

በአስረጅነትእንዲሁም ሦስቱ የሕዝብ ታዛቢዎች ተገኝተው በፊርማቸው አረጋግጠዋል፡፡

ውሣኔውንም በግንባር ቀርበው እንዲረከቡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፓርቲያችሁ ዕጩዎች በተደጋጋሚ ጥሪ ቢደረግላቸውም ቀርበው ለመውሰድ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ቦርዱ ከምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ እና ከዞኑ የምርጫ ክልሎች አስተባባሪ ሪፖርት ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ ፓርቲያችሁ ጉዳዩን ለቦርዱ ባቀረበው መሠረት ጽሕፈት ቤቱ የዞኑ የምርጫ ክልሎች አስተባባሪ ስፍራው ድረስ በመገኘት ተጠቃሾቹ ዕጩዎች የቋንቋ መስፈርቱን ለማሟላታቸው በግንባር እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ቢነገራቸውም ለመቅረብ ፍቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን እና ይህንኑ ጉዳይ የዞኑ የምርጫ ክልል አስተባባሪ አቶ ሁሴን ቲፎ ለአቶ ማኅተመ በኩረ የምስራቅ ሸዋ ዞን የመኢአድ አስተባባሪ በስልክ ነግረዋቸው እሳቸውም በተደጋጋሚ ዕጩዎቹን በስልክ ለማግኘት ሞክረው ስላልቻሉ ምንም ማድረግ አንችልም ትተነዋል ማለታቸውን አረጋግጠናል፡፡

የዞኑ የምርጫ ክልሎች አስተባባሪ ሪፖርት ለሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ በቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት የፖለቲካ ፓርቲዎችና የምርጫ ተወዳዳሪዎች መምሪያ በኩል በግንባር ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለሆነም ላቀረብነው አቤቱታ መልስ አልተሰጠም ያላችሁት ከእውነት የራቀ ነው፡፡

**በተራ ቁጥር** 11. የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/591/2002 በወላይታ ዞን ለምርጫ ክልል 2 ፓርቲያችን ባቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ላይ የምርጫ አስፈፃሚዎች ስላደረሱት በደል ላቀረብነው አቤቱታ መልስ አልተሰጠም ብላችኋል፡፡

ለዚሁ መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር አ573/ፖአ/ጠ1521 በተፃፈ ደብዳቤ ማጣራት ተደርጎ ምላሽ የተሰጣችሁ መሆኑን ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

**በተራ ቁጥር** 12. መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/634/2002 በተፃፈ ደብዳቤ ላቀረብነው አቤቱታ እንደሚመዘገቡ ከቦርዱ ጋር ስምምነት የተደረሰ ቢሆንም ተፈፃሚ ሳይሆን ቀርቷል ብላችኋል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ራሳቸውን ያገለሉ ዕጩዎችን ለመተካት በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በኩል ለቦርዱ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ተጨማሪ የመተኪያ ጊዜ ተሰጥቷችሁ በቦርዱ በኩል የቅርብ ክትትል እየተደረገ ዕጩዎቻችሁን እንድታስመዘግቡ መደረጉ በይፋ የሚታወቅ ነው፡፡

ፓርቲያችሁም በወቅቱ ለዚሁ የቦርዱ ቀና ምላሽ ለሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ እና ለቦርዱ በግንባር ጭምር ምስጋናችሁን አቅርባችኋል፡፡

በዚህም ፓርቲያችሁ በየምርጫ ክልሉ በተለያዩ ምክንያቶች የለቀቁ ዕጩዎቹን በመተካት ያስመዘገባቸው ዕጩዎች ብዛት ከመድረክ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ቦርዱ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ስለሆነም ተፈፃሚ ሳይሆን ቀረ ያላችሁት ከእውነት የራቀና ተገቢው መፍትሔ ተሰጥቶት ያለፈ መሆኑን ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችም ጭምር ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡

**በተራ ቁጥር** 13. መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መለ/3/658/2002 በፃፋችሁት ደብዳቤ በቦርዱ እስከአሁን መልስ አልተሰጠም ብላችኋል፡፡

በመሠረቱ በተጠቀሰው ደብዳቤ የቀረቡት ጥያቄዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከየምርጫ ክልሉ የለቀቁ ዕጩዎችን በመተካቱ አካሄድ ላይ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና

በቦርዱ ከተደረሰበት ስምምነት ውጪ የዕጩ ምዝገባ እንዲደረግላችሁ ያቀረባችሁት ጥያቄ ነው፡፡ ይኸውም በዕጩዎች ምዝገባ ወቅት ከሕግ ውጪ መስፈርቱን ሳያሟሉ ለመመዝገብ ጥያቄ አቅርበው ተቀባይነት ያላገኙትን ዕጩዎች ድጋሚ በመተካት ስም በቦርዱ በተሰጠው ጊዜ ለማስመዝገብ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል በዕጩዎች ምዝገባ ወቅት በሕጉ መሠረት በየደረጃው ውሣኔ የተሰጠበት ስለሆነ ተቀባይነት እንደሌለው በተደጋጋሚ ተገልፆላችኋል፡፡

ይህንኑ አቤቱታ በተመለከተ በተደጋጋሚ በጋራ ምክር ቤቱ በኩል ተመላልሶ እየቀረበ የቦርዱ ኃላፊዎች የእናንተ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ባሉበት የማጣራት ውጤቱን ማለትም ከሕግ ውጪ የቀረበ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ስለሆነም መልስ አልተሰጠንም የሚለው አገላለፅ ከእውነት የራቀ ነው፡፡

**በተራ ቁጥር** 14. ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር 699/2002 በተፃፈ ደብዳቤ የደረሰባችሁን የስነልቦና ጫና ገልፃችኋል፡፡

በመሠረቱ አንድ ሰው በዕጩነት ለመመዝገብ በምርጫ ሕጉ የተደነገጉትን መስፈርቶች ማሟላት ግዴታው ነው፡፡ መስፈርቱን ለማሟላቱ ደግሞ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ዕድሜው 21 ዓመት ለመሙላቱ ማንኛውም አይነት ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለን እጩ አለመመዝገቡ አግባብነት አለው፡፡ ይሁን እንጂ ዕጩው ዕድሜው 25 ዓመት ሊሆነው እንደሚችል የሕክምና ማስረጃ አያይዞ በማቅረቡ ያለምንም ውጣ ውረድ እንዲመዘገብ መደረጉ ቦርዱን ሊያስመሰግነው ይገባል፡፡

ይህም ሂደት በየትኛውም ወገን ላይ የስነልቦና ጫና ሊፈጥር የሚችልበት ሁኔታ ግልፅ ሆኖ አይታይም፡፡

**በተራ ቁጥር** 15. ግንቦት 7 ቀን 2002 ዓ.ም. በደብዳቤ ቁጥር 739/2002 በተፃፈ ደብዳቤ ባቀረብነው ግምገማ የምርጫ ስነምግባሩ አዋጅ ቁጥር 662/2002 መጣሱን አመልክተን አስቸኳይ እርምት እንዲደረግ ላቀረብነው ደብዳቤ 14 ገፅ ተጨባጭ ማስረጃ አያይዘን አቅርበናል ብላችኋል፡፡

ለዚሁ ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር አ573/ፖአ/ጠ1596 በፃፍንላችሁ ደብዳቤ ቦርዱን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አጣርተን ተገቢውን እርምት ለማድረግ ማስረጃዎችን እንድትልኩልን በአክብሮት ጠይቀናችኋል፡፡

ይህንን ጥያቄ ቦርዱ ያቀረበው ተያይዟል ያላችሁት 14 ገፅ ማስረጃ ሳይሆን የክሱ ዝርዝር ማብራሪያ ሆኖ ስላገኘው ነው፡፡

በመጨረሻም ግንቦት ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር 754/2002 ባቀረባችሁት አቤቱታ ገፅ 5 ምርጫው ነፃና ፍትሐዊ ያለመሆኑን ገልፀን በየምርጫ ክልሉ አቤቱታችን ለማቅረብ ሞክረን ከምርጫው ፍፃሜ ሰዓት ጀምሮ የየክልሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች በቦታቸው ባለመገኘታቸው እና አቤቱታችንም ሀገር አቀፍ ያሉትን ሁሉንምን የምርጫ ክልሎች የሚያጠቃልል በመሆኑ በተሻሻለው የምርጫ ሕግ መሠረት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቅርበናል ብላችኋል፡፡

በመሠረቱ፣

1. የቀረቡት አቤቱታዎች ከምርጫው ቀን በፊት በተከሰቱ ጉዳዮች ላይ ሆኖ ሳለ፣
2. በምርጫው ዕለት ለተከሰቱ ጉዳዮችም የምርጫ ሕጉ ያስቀመጠው የአቤቱታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት እንዳለ እየታወቀ በዚሁ መሠረት መፍትሔ ማግኘት ሲቻል

ከምርጫው ፍፃሜ በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ማፈላለግ በሕጉም ቢሆን አግባብነት የሌለው መሆኑን ቦርዱ ተገንዝቧል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ ያቀረባችሁትን አቤቱታና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ የጠየቃችሁትን ቦርዱ ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. ባካሄደው 145ኛ አስቸኳይ ስብሰባው በስፋትና በጥልቀት ተወያይቶ ትዕዛዝ ከማስተላለፉም በላይ ግንቦት 27 ቀን 2002 ዓ.ም. ባካሄደው 146ኛ አስቸኳይ ስብሰባው በጥልቀት እና በስፋት መርምሮ በማስረጃ ለማስደገፍ ባለመቻላችሁ ጥያቄያችሁን ያልተቀበለው መሆኑን በአክብሮት እገልፃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>እንዲያውቁት፣</u>

- ለክቡር ፕሮፌሰር መርጋ በቃና
  የቦርዱ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ፣</u>